## ማውጫ

ገጽ

ምዕራፍ I:- መግቢያ:- ........................................................................................1

ምዕራፍ II:- አጠቃላይ መመሪያ:- ...........................................................................2

ምዕራፍ III:- መጠይቁን ማረም:- ...........................................................................5

ክፍል 1: ዓምድ 1-9ሐ የተመረጠው ቤተሰብ አድራሻና የቅ/ጽ/ቤት መለያ:- ..........5

ዓምድ 1-3 ክልል፣ዞን፣ወረዳ:- ..............................................................................5

ዓምድ 4 ከተማ:- ..............................................................................................5

ዓምድ 5 ከፍተኛ/ወረዳ/ክፍለ ከተማ :- ...............................................................6

ዓምድ 6: ቀበሌ፣ ..............................................................................................6

ዓምድ 7:-የቆጠራ ቦታ ......................................................................................6

ዓምድ 8: የተመረጠው ቤተሰብ ምርጫ ተራ ቁጥር:- ...............................................6

ዓምድ 8ሀ:-የቤተሰብ ኃላፊ ሙሉ ስም .................................................................6

ዓምድ 9ሀ:-ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ................................................................................6

ዓምድ 9ለ: የቆጠራ ቦታ ተከታታይ ተራ ቁጥር ...................................................6

ዓምድ 9ሐ:-የቀጠለ መጠይቅ አለ? ......................................................................6

*ክፍል 2 ስለ ቤተሰቡ አባላት ዝርዝር መረጃ /ከዓምድ 10-20/ :- ................................6*

ዓምድ 10 የቤተሰብ መደበኛ አባላት ተራ ቁጥር:- ...................................................6

ዓምድ 11 የቤተሰብ መደበኛ አባላት ሙሉ ስም:- .....................................................7

ዓምድ 12 ከቤተሰቡ ኃላፊ ጋር ያላቸው ዝምድና .....................................................7

ዓምድ 13 ጾታ :- ..............................................................................................7

ዓምድ 14 ዕድሜ :- ...........................................................................................7

ዓምድ 15-16 የትምህርት ሁኔታ:- .....................................................................7

ዓምድ 15 ማንበብና መጻፍ ይችላሉ?:- ................................................................7

ዓምድ 16 የጨረሱት ከፍተኛ ክፍል ስንተኛ ነው ?:- .............................................8

ዓምድ 17-19 የስልጠና ሁኔታ:- .........................................................................8

ዓምድ 17 የሙያ የቴክኒክ ስልጠና ወስደው ያውቃሉ? ..........................................8

ዓምድ 18 የሰለጠኑበት የሙያ/የቴክኒክ ስልጠና ዓይነት ምንድነው ?:- ...................8

ዓምድ 19 ስራዎን የሚሰሩት በሠለጠኑበት ሙያ/መስክ ነውን ? ካልሆነ ለምን ? ...........................................................................................................10

ዓምድ 20 የጋብቻ ሁኔታ:- ..............................................................................10

ክፍል 3:- የመጠይቁ ክፍል 3 አሞላል መመሪያ፣ያለፉት 6 ወራት የሥራ ሁኔታ:-......10

ዓምድ 21-26 /ዕድሜያቸው 10 ዓመትና በላይ ለሆናቸው ብቻ/

ዓምድ 21 ባለፉት 6 ወራት ውስጥ ለጥቂት ጊዜም እንኳን ቢሆን በምርታማ ሥራ ማለትም ተቀጥረው በክፍያ ወይም ትርፍ ለማግኘት ወይም ለቤተሰብዎ ገቢ በሚያስገኝ ሥራ ተሰማርተው ነበር?:- ....................10

ዓምድ 22 ባለፉት 6 ወራት ውስጥ ለጥቂት ጊዜም ቢሆን ሥራ ለማግኘት/ለመስራት ዝግጁ ነበሩ? ....................11

ዓምድ 23 በ------ወር በምን ያህል ሳምንት በምርታማ ሥራ ላይ ተሰማርተው ነበር? ወይም ደግሞ ለምን ያህል ሳምንት ሥራ አጥ ነበሩ፣ ፍላጐትም ነበረዎት ? ....................11

ዓምድ 24 ሥራ ሳይኖርዎት ቆይተው ባለፉት 6 ወራት ውስጥ የጀመሩት ሥራ ነበርን ?- ....................11

ዓምድ 25 በዓምድ 23 ባለፉት 6 ወራት ሥራ ላይ/ ሥራ አጥ የነበሩበት አጠቃላይ የሳምንታት ድምር ....................11

ዓምድ 26 ባለፉት 6 ወራት ከ13 ሳምንት በላይ ሥራ ያልሰሩበት ወይም ሥራ ለመሥራት ዝግጁ ያልነበሩበት ምክንያት ምንድነው ?:- ....................12

ምዕራፍ 4:- የመጠይቁ የክፍል 4 አሞላል መመሪያ ያለፉት 7 ቀናት የሥራ ሁኔታ:- 12

ዓምድ 27-43 /ዕድሜያቸው 10 ዓመትና በላይ ለሆናቸው/....................

ዓምድ 27 ባለፉት 7 ቀናት ውስጥ በምርታማ ሥራ ማለትም ተቀጥረው በክፍያ ወይም ትርፍ ለማግኘት ወይም ለቤተሰብዎ ገቢ በሚያስገኝ ሥራ ተሰማርተው ነበር? ....................12

ዓምድ 28 የምሣና የጉዞ ሰዓትን ሳይጨምር ባለፉት 7 ቀናት በሰሯቸው በሁሉም ስራዎችዎ ለስንት ሰዓት ሰርተዋል ? :- ....................12

ዓምድ 29 ባለፉት 7 ቀናት የሠሩት የሥራ ሰዓት ድምር ስንት ነው ?:- ....................13

ዓምድ 30 ሥራ እያሎዎት ነበር ባለፉት 7 ቀናት በሥራ ላይ ያልተሰማሩት? :- 13

ዓምድ 31 - 33 የሥራ ዓይነት: የድርጅት ዋና ምርት/አገልግሎት: የቅጥር ሁኔታ/employment status/ ....................13

ዓምድ 31 ባለፉት 7 ቀናት የሠሩት የዋነኛ ሥራዎ ዓይነት ምንድነው? :- ....................13

ዓምድ 32 በዋነኛነት የሚሰሩበት ድርጅት ዋና ምርት ወይም የሚሰጠው አገልግሎት ዓይነት ምንድነው ? :- ....................14

ዓምድ 33 የዋነኛ ሥራዎ የቅጥር ሁኔታ/employment status/ ምንድነው? :- ....................14

ዓምድ 34 - 38 ከቅጥር ሥራ የተገኘ ክፍያ ....................15

ዓምድ 34 ለሥራዎ የሚከፈልዎት በገንዘብ ነው ወይስ በዓይነት ? :- ....................15

ዓምድ 35 ለዋናው ሥራዎ የአከፋፈል ጊዜ እንዴት ነው ? ....................15



\\Csa02\Survey\continious Labour force Urban round 1\Metadata\Urban Round 2-2003\Manual\Editing & Coding Manual.doc

ዓምድ 36 በገለፁልኝ የአከፋፈል መሠረት ባለፈው ወር ለስንት የአከፋፈል ጊዜያት ሠርተዋል?:- ....15
ዓምድ 37 በዓምድ 35 በገለፁልኝ አከፋፈል መሠረት ለመጨረሻ ጊዜ ምን ያህል ተከፈልዎት? ....16
ዓምድ 38 በዋነኛነት ለሰሩት ሥራ ባለፈው አንድ ወር ውስጥ ምን ያህል ተከፈልዎት:- ....16
ዓምድ 39 ድርጅቱ/ የሥራ መስኩ አሥርና በላይ ሠራተኞች አሉት ወይም የተሟላ የሂሣብ መዝገብ ይይዛል ወይም ፈቃድ አለው? :- ....16
ዓምድ 40 አብዛኛውን ጊዜ በሳምንት ስንት ሰዓት ይሠራሉ?:- ....16
ዓምድ 41 - 42 ከፊል ሠራተኝነት ....17
ዓምድ 41:- ባለፈው ሳምንት ተጨማሪ ሰዓት ለመሥራት አቅምም ፍላጐትም ነበረዎት? ....17
ዓምድ 42:- ተጨማሪውን ሰዓት በምን ዓይነት ሥራ መሰማራት ይፈልጉ ነበር? 17

ምዕራፍ 5:- የመጠይቁ ክፍል 5 አሞላል መመሪያ ሥራ አጥነትና ሥራ አጦች ባህሪይ፣ ዓምድ 43-52 /ዕድሜያቸው 10 ዓመትና በላይ ለሆናቸው ብቻ/
ዓምድ 43:- ባለፉት 3 ወራት ሥራ ለማግኘት ወይም የግል ስራ ለመጀመር ጥረት አድርገው ነበር?:- ....17
ዓምድ 44:- ሥራ ለማግኘት ወይም ለመጀመር ምን ጥረት አደረጉ? :- ....18
ዓምድ 45 ለምንድነው ስራ ለመስራት ወይም ለማግኘት ጥረት ያላደረጉት ? ....18
ዓምድ 46:- በሚቀጥለው 1 ወር ውስጥ ገቢ የሚያስገኝ ሥራ ቢያገኙ ይሰራሉ?.18
ዓምድ 47:- በአቅምዎ ተቀጥረው ሊሠሩት የሚችሉት ሥራ ቢገኝልዎት ወይም በግል ሥራ ለመሰማራት አስፈላጊ ነገሮች ቢሟሉ ሥራ ለመጀመር ዝግጁ ነዎት? ....18
ዓምድ 48:- ለምንድነው ሥራ ቢያገኙ የማይሠሩት? ....18
ዓምድ 49:- የሚፈልጉት ሥራ ምን ዓይነት ነው ?:- ....19
ዓምድ 50:- የግል ሥራ/ የራሥዎን ድርጅት ለማቋቋም የገጠሞት/ የሚገጥሞት ችግር አለ ? ካለ ምንድን ነው ?:- ....19
ዓምድ 51:- ለምን ያህል ወራት ያለ ስራ ቆይተዋል? ....19
ዓምድ 52:- ከዚህ በፊት በቅጥር ወይም በግል ሥራ ሠርተው ያውቃሉ ? ....19

ዕዝል:- የጥናቱ ቅጾችና መጠይቅ ....20


\\Csa02\Survey\continious Labour force Urban round 1\Metadata\Urban Round 2-2003\Manual\Editing & Coding Manual.doc

# የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለስልጣን

## የ1996 ዓ.ም. የከተማ ተከታታይ የሥራ ሥምሪት ሁኔታ ጥናት መጠይቅ

## እርማትና ኮድ አሰጣጥ መመሪያ

አዲስ አበባ
ግንቦት 1996 ዓ.ም.


\\Csa02\Survey\continious Labour force Urban round 1\Metadata\Urban Round 2-2003\Manual\Editing & Coding Manual.doc

# የ1996 ዓ.ም. የከተማ ተከታታይ የሥራ ሥምሪት ጥናት
# የመጠይቅ ዕርማትና ኮድ አሰጣጥ መመሪያ
# ምዕራፍ 1

## መግቢያ

የአንድ አገር ኢኮኖሚያዊ ማህበራዊና ፖለቲካዊ እድገት ለማምጣት የመረጃ ፋይዳ ቀላል ግምት የሚሰጠው አይደለም:: በመሆኑም መንግሥት ወቅታዊና ጥራት ያላቸውን ስታቲስቲካዊ መረጃዎች ቢቻል በሁሉም መልክ፣ እንዲሰበሰብለት ይፈልጋል ከነዚህም የመረጃ ዓይነቶች መካከል የአንድ አገር ህዝቡ የሥራ ስምሪትና ተዛማጅ መረጃዎች ማለትም ለሥራ የደረሰ፣በስራ ላይ የተሰማራ፣ ስራ አጥ የሆነ፣ በስራ ላይ ለተሠማሩት የሥራ ዓይነት፣የሥራ ሰዓት፣... ወዘተ ናቸው::

በዚህም መሠረት የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለስልጣን በጥቅምት ወር ላይ የመጀመሪያውን 1996 ዓ.ም. ተከታታይ የሥራ ስምሪት ጥናት መጃ ሰብስቧል:: መረጃ ከመስክ ከመሰብሰቡ በፊት ለመረጃ ሰብሳቢዎችና ተቆጣጣሪዎች በቂ ስልጠና የተሰጠ በመሆኑና በመስክ ላይም አስፈላጊ የጥራት ቁጥጥር የተካሄደ ቢሆንም የመረጃውን ጥራት ይበልጥ ከፍ ለማድረግና በመስክ ሥራ ወቅት ሳይታዩ ያለፉ ስህተቶች ሊኖሩ ይችላሉ:: በተጨማሪም በመስክ ሥራ ወቅት ኮድ ያልተሞላላቸው ጥያቄዎች፣ እንደ የሥራ ዓይነት የመሳሰሉ ጥያቄዎች በመስክ ላይ ኮድ ቢሞላላቸውም በቢሮ እንደገና ማረጋገጥ አስፈላጊ ይሆናል:: የጥናቱ መረጃ ይበልጥ ጥራት እንዲኖረውና ግቡን እንዲመታ አስተዋፅኦ ከሚያደርጉት ሥራዎች መካከል አንደኛው ከመስክ የሰበሰቡትን መረጃዎች በሚገባ አርሞና ኮድ ሰጥቶ ለሚቀጥለው የሥራ ክፍል ማስተላለፍ ነው:: ስለሆነም፣ የኮድ አሰጣጥና እርማት የማድረግ ተግባር በጥንቃቄ መከናወን ይኖርበታል:: በዚህ ጥናት የተካተቱት ጥያቄዎች ሰፋ ያለ ስለሆነና የጥያቄዎቹ ዓይነት በመስክ ላይ ኮድ የሚደረጉ መሆናቸው በእርማቱና ኮድ አሠጣጡ ላይ ብዙ ጫና እንደሚፈጥር ይገመታል:: ይሁን እንጂ ጥያቄዎችን በቀላሉ እርስ በእርስ ለማመሳከር ይቻለው ዘንድ አራሚው ስለጥናቱ በቂ እውቀት ሊኖረው ይገባል:: ለምሳሌ :- የሥራ ዓይነትና የድርጅት ዋና ምርት ወይም አገልግሎት ዓይነት መረጃ ኮድ ሲደረግ በመጠይቁ የተሞሉትን መረጃዎች በጥሞናና በእርጋታ ማየትና መረዳትን ይጠይቃል:: ስለሆነም፣ በመጠይቁ እርማትና ኮድ መስጠት ሥራ የሚሳተፉ ሠራተኞች የጥናቱን ውጤት በማሻሻል ረገድ ከፍተኛ የሥራ ድርሻ የተጣለባቸው መሆኑን አውቀው የእርማትና ኮድ አሰጣጡን መመሪያ በደንብ መረዳት ይጠበቅባቸዋል::


\\Csa02\Survey\continious Labour force Urban round 1\Metadata\Urban Round 2-2003\Manual\Editing & Coding Manual.doc

ይህ ጥናት በ527 የከተማ ቆጠራ ቦታዎች የተካሄደ ሲሆን፣ በያንዳንዱም ቆጠራ ቦታ 30 ቤተሰቦች በናሙና ተመርጠው መረጃ ተሞልቶላቸዋል::

# ምዕራፍ II

## <u>አጠቃላይ መመሪያ</u>

ሀ. <u>ኤዲቲንግ:</u>

ከልዩ ልዩ ጥናቶች የሚሰበሰቡትን መረጃዎች ኤዲት ማድረግ /ማረም/ የመረጃውን ጥራት ለመገምገምና እንደዚሁም ስህተቶችን፣ የሚቃረኑ መረጃዎችን፣ ሳይሞሉ የቀሩትን፣ ...ወዘተ በማረም የመረጃውን ጥራት ለማሻሻል ይረዳል::

ኤዲቲንግ ማለት የተሰበሰበውን መረጃ ሁኔታ በመመልከት በተሰጠው መመሪያ መሠረት አስፈላጊውን እርማት ማድረግ ነው:: ኤዲተሩ /አራሚው/ ይህንን ሥራ በሚያከናውንበት ወቅት የመረጃ መሰብሰቢያው ፎርም /መጠይቅ/ ለመረጃ ሰብሳቢው በተዘጋጀው መመሪያ መሠረት መሞላቱን ማረጋገጥ ይገባዋል:: ኤዲተሩ /አራሚው/ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል::

1. <u>ሳይሞሉ የቀሩ መረጃዎች</u>

በመጠይቁ ሳይሞሉ የቀሩትን መረጃዎች በመፈለግ መመሪያውን በመከተል አስፈላጊውን እርማት ማድረግ ነው:: ሣይሞሉ በቀሩ መረጃዎች ፋንታ የሚሞላው መረጃ የሚገኘው ሌሎች የተሞሉ መረጃዎችን በማገናዘብና በመመርመር ነው:: በተቻለ መጠን ለተዘለሉና ሣይሞሉ ለቀሩ መረጃዎች በሙሉ አስፈላጊው እርማት ተደርጐ መሙላት የሚያስፈልግ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል:: ሆኖም ሣይሞሉ ለቀሩት መረጃዎች በፎርሙ /መጠይቁ/ ከታዩት መረጃዎች አኳያ አመሳክሮና መርምሮ ለማረም የማይቻል ከሆነ በፈጠራ መሙላት ስለማይገባ ሣያርሙ ዓምዱን ባዶውን መተው ይመረጣል:: የዚህ ዓይነት ሁኔታ ኮድ ሲደረግ ላልታወቀ መልስ የሚሰጠው ኮድ ይሰጠዋል ማለት ነው::

2. <u>ሊሆኑ የማይችሉና የማይመስሉ መልሶች</u>

ሊሆኑ የማይችሉ መልሶችና የማይመስሉ መልሶችን በእርማት ጊዜ ማስወገድ ያስፈልጋል:: ሊሆኑ የማይችሉ መልሶች በመመሪያው ከተሰጠው ውጭ የተመለሱ መልሶች ሲሆኑ <u>ለምሳሌ፣</u> ባለፈው ሳምንት ለስንት ቀናት ሠሩ? የሚል ጥያቄ ቢኖርና በዓምዱ የሰፈረው ቀናት ብዛት ከ7 ቀን በላይ ከሆነ ይህ


\\Csa02\Survey\continious Labour force Urban round 1\Metadata\Urban Round 2-2003\Manual\Editing & Coding Manual.doc

ሊሆን የማይችል መልስ በመሆኑ መታረም አለበት:: የማይመስሉ መልሶችን በተመለከተ የጋብቻ ሁኔታን እንደ ምሣሌ ብንወስድ የአንድ ሰው የጋብቻ ሁኔታ፣

1/ ፈጽሞ ያላገባ/ያላገባች

2/ ያገባ/ያገባች

3/ ባል/ሚስት የሞተባት/የሞተችበት

4/ የተፋታ/የተፋታች 5 የተለያዩ

ሲሆን ይህም መረጃ የሚሞላው ዕድሜአቸው 10 ዓመትና በላይ ለሆኑ ለቤተሰብ አባላት በሙሉ ነው:: ለአንድ ዕድሜው 11 ዓመት ለሆነ ልጅ የጋብቻ ሁኔታ "ሚስት የሞተችበት" ተብሎ ቢሞላ በዚህ ዕድሜው አግብቶ ሚስቱ ልትሞትበት ስለማይችል መልስ ሊሆን የማይችል በመሆኑ መታረም አለበት:: እርስ በእርሳቸው የሚቃረኑ መልሶች ተመዝግበው ሲገኙ ከቀሩት ዓምዶች ጋር በማገናዘብ መረጃው ይታረማል::

<u>የሚቃረኑ መልሶች</u> በተለያየ ዓምድ ላይ የተሞሉ መረጃዎች ለምሳሌ በዓምድ 15 እና 16 ላይ ስለትምህርት የተሞላው መረጃ መልስ ሰጪው በአዲሱ የትምህርት ሥርዓት 10ኛ ክፍልን እንዲሁም በቀድሞ 12ኛን እንኳ ያልጨረሰ ቢሆንና በዓምድ 18 ላይ የስልጠናው ዓይነት ኘሮፌሽናል ቢሆን የሚቃረኑ ስለሆኑ ማረም ተገቢ ነው:: የሚቃረኑ መልሶች የሚባሉት ከሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ መልሶች ሳይዛመዱ ሲቀሩ ነው::

4 <u>ጽሁፉን ለማንበብ የሚያስቸግሩ መልሶች</u>

በትክክልና በደንብ የማይነበቡ መልሶችን ማረምና ማስተካከል ያስፈልጋል:: በተጨማሪም እርማቱ በሚደረግበት ወቅት የሚፃፉ ጽሁፎች ሁሉ በደንብና በቀላሉ የሚነበቡ መሆናቸውን መገንዘብ ያስፈልጋል::

5. <u>ከመመሪያ ውጭ ስለተሞሉ መልሶች /የይለፍ ትዕዛዞች ካልተከበሩ/</u>

ለምሳሌ ባለፉት 7 ቀናት ውስጥ ሥራ ሠርተዋል? ተብለው ለተጠየቁት መልስ "የለም" ብለው ኮድ "2" ለተሞላላቸው በሚቀጥለው ዓምድ የሥራ ሰዓት ተሞልቶ ከተገኘ የነዚህ ዓምዶች መልስ የሚቃረኑ መልሶች ናቸው:: ይህም ማለት በሳምንት ውስጥ ምንም ሥራ ያልሰራን ሰው ስንት የሥራ ሰዓቶች ሠራህ ብሎ መጠየቅ አስፈላጊ አይደለም:: ነገር ግን በመጀመሪያው ዓምድ ላይ የተሞላው ኮድ "2" የለም የሚለውን ስህተት ሊሆን ስለሚችል ተከታታይ ዓምዶችን መርምሮ ማየት አስፈላጊ ይሆናል::

በዚህ ጥናት ከመመሪያ ውጭ የተሞሉ መረጃዎች ሊያጋጥሙ ስለሚችሉ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል:: ለምሳሌ የስልጠናና የጋብቻ ሁኔታ የሚጠየቀው ዕድሜያቸው 10 ዓመትና በላይ ለሆናቸው የቤተሰብ አባላት ብቻ

ነው፡፡ ስለዚህ ዕድሜው 9 ዓመት ለሆነው ህፃን የስልጠናና የጋብቻ ሁኔታ ተሞልቶለት ቢገኝ ምንም እንኳ ዕድሜያቸው 9 ዓመትና በታች የሆኑ ህፃናት መመሪያው ዕድሜያቸው 10 ዓመት እስካልሞላ ድረስ ስለስልጠና ጋብቻ ሁኔታ የሚያመለክቱ መረጃዎች እንደማይጠበቅባቸው ስለሚገልጽ የተሞላው መረጃ ከመመሪያ ውጭ ስለሆነ መሠረዝ ይኖርበታል፡፡ በተጨማሪም የዓምዶችን ቅደም ተከተል ለማመልከት መረጃዎች ሲሞሉ ከየትኛው ዓምድ ወደ የትኛው ማለፍ እንደሚገባ በመጠይቁ ላይ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ስለሆነም መረጃዎች ይህንኑ ተከትለው መሞላት ስለሚገባቸው በመጠይቁ ላይ በተመለከተው መሠረት ያልተሞሉ መረጃዎች ከተገኙ መታረም ይኖርባቸዋል፡፡ ለምሳሌ ዓምድ 27 ኮድ 2 ከተሞላ እስከ ዓምድ 29 ያሉት ጥያቄዎች በሠረዝ መታለፍ ይኖርባቸዋል፡፡ ነገር ግን ዓምድ 28 እና ዓምድ 29 ተሞልቶ ከተገኘ ዓምዶችን በማገናዘብ ማስተካከልና ማረም ያስፈልጋል፡፡

6. በጽሑፍ የተሰጠ መልስና ኮድ አለመጣጣም

በመጠይቁና በመመሪያው ውስጥ በግልጽ እንደተመለከተው ለአሠራር ያመች ዘንድ መረጃዎች በኮድ ብቻ (ከጥቂት ዓምዶች በስተቀር) እንዲገለጽ ተደርጓል፡፡ሆኖም አንዳንድ መረጃ ሰብሳቢዎች በስህተት መልሶቹን በቃላትና በኮድ ሊመዘግቡ ይችላሉ፡፡ ይህ አሠራር በተለይ መረጃዎች በኮምፒውተር በሚቀነባበሩበት ወቅት ችግር ስለሚፈጥሩ በቃላት የተመዘገቡትን መረጃዎች ከሚጣጣመው ኮድ ጋር ተገናዝቦ መሞላት ይገባዋል፡፡ስለዚህ በጽሑፍና በኮድ የተሰጠው መልስ ሲለያይ ሌሎች ተዛማጅ ዓምዶችን መመልከት ተገቢውን እርማት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

ለ. <u>ኮዲንግ፡-</u>

ኮዲንግ ማለት በፎርሙ የተሰጡትን መልሶች ወደ አሀዝ መለወጥ ነው፡፡ ይህም አሀዝ በቀላሉ መረጃውን በኮምፒውተር ለማቀነባበር ይረዳል፡፡ የእርማትና (Editing) የኮድ የማድረግ ተግባር በማጣመር ይካሄዳል፡፡ በዚህ ፎርም የተሞሉት መረጃዎች በአብዛኛው አስቀድመው ኮድ ተደርገዋል፡፡ <u>ለምሳሌ</u> ጾታ፣ ዕድሜ፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ ...ወዘተ ናቸው፡፡ ለነዚህ መልሶች የእርማት ተግባር ለማከናወን ኮዶቹ በመመሪያው መሠረት መሞላታቸውን ማረጋገጥ ብቻ ነው፡፡ እንደ አዲስ ኮድ መደረግ ያለባቸው መልሶች ደግሞ በክፍል 1 የተገለፁት የአካባቢ መለያ መልሶች ናቸው፡፡ እነዚህን መልሶች ኮድ ለማድረግ የሚረዱ የኮድ ዝርዝር ይሰጣል፡፡ ይህ የኤዲቲንግ ኮዲንግ መመሪያም የአሠራሩን ሁኔታና ዘዴ የሚገልጽ ጽሁፍ ነው፡፡

- የእርማቱና ኮድ አሰጣጡ ሥራ መከናወን ያለበት ለዚሁ በተዘጋጀው መመሪያ መሠረት መሆን እንዳለበት ማስታወስ ይገባል፡፡ አንዳንድ በዚህ መመሪያ ውስጥ ያልተጠቀሱ ነገሮች ሲያጋጥሙ ጥያቄዎቹን


\\Csa02\Survey\continious Labour force Urban round 1\Metadata\Urban Round 2-2003\Manual\Editing & Coding Manual.doc

ለሚመለከተው ተቆጣጣሪ በማቅረብ መፍትሔ እንዲሰጠው ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

- ሥራውን ለማከናወን መነሻው በመስክ የተሞላው መረጃ ስለሆነ አስቀድሞ እያንዳንዱ መጠይቅ መሞላቱንና ተሟልቶ መምጣቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ በአንድ ቆጠራ ቦታ ለ30 ቤተሰቦች መረጃ ተሞልቶአል፡፡ ለእያንዳንዱ ቤተሰብም አንድ ባለ 4 ገጽ /A3 Size/ መጠይቅ የተሞላ ሲሆን፣ ተጨማሪ መጠይቅም ተሞልቶላቸው ከሆነ ሁለት ባለ 4 ገጽ መሆኑን መረዳት ተገቢ ነው፡፡ ከዚህም ሌላ አንዳንድ በመረጃው አሰባሰብ ጊዜ ያጋጠሙትን ሁኔታዎች የሚያብራሩና ከመጠይቁ ጋር ተያይዘው የመጡ አስተያየቶችን በሚገባ መያያዛቸው ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

- እርማት በሚደረግበትና ኮድ በሚሰጥበት ጊዜ ሁሉ ሥራው ከሚመለከተው ኃላፊ ካልታዘዘ በስተቀር ማንኛውም በመረጃ ሰብሳቢው የሰፈረው ነገር መፋቅ/መጥፋት የለበትም፡፡ መረጃውን እርማት የሚያደርግበት ከሆነ ካሰፈረው መረጃ አጠገብ መረጃው ከተፃፈበት ቀለም በተለየ ቀለም እርማቱ ይደረጋል፡፡

## <u>ምዕራፍ</u> III

## <u>መጠይቁን ማረም</u>

### ክፍል 1 <u>የተመረጠው ቤተሰብ የአካባቢ መለያ</u>

ከዓምድ1 እስከ ዓምድ 8 ያለውን የክልል፣ ዞን፣ ወረዳ፣ ከተማ፣ ከፍተኛ/ወረዳ/ ቀበሌ ስሞች በመጠይቁ ሽፋን ገጽ ላይ እና በየመጠይቆቹ አናት ላይ ተሞልተዋል፡፡ እነኚህ ከክልል እስከ ቀበሌ ላሉት ዓምዶች ካርድ ኮለሞቹ <u>መስክ ላይ ያልተሞሉ ስለሆነ፣</u> በተለይ ተዘጋጅቶ የቀረበውን የአካባቢ መለያ ኮድ መጽሐፍ በመጠቀም ካርድ ኮለሞቹን መሙላት ያስፈልጋል፡፡ የቆጠራ ቦታ ኮድ በትክክል መሠጠቱን ማገናዘብ ያስፈልጋል፡፡ እንዲሁም ጥናቱ የተካሄደበት የቅ/ጽ/ቤት ስምና ኮድ እና ለቆጠራ ቦታ ተከታታይ ቁጥር የሚሰጥበት ካርድ ኮለም መሞላት አለባቸው፡፡ ተጨማሪ መጠይቅ መኖሩ አለመኖሩ በተከታይ ዓምድ በማየት ማረጋገጥ ይሆናል፡፡

<u>ዓምድ 1-3</u> :- <u>ክልል፣ዞን፣ወረዳ</u>:- ጥናቱ የሚካሄድበት ክልል፣ዞንና ወረዳ ስም በዓምዱ በተሰጠው ቦታ በትክክል መሞላቱን ማረጋገጥ አለበት፡፡ በካርድ ኮለሞቹ /Area Code Book/ ተስማሚው ኮድ ይሞላል፡፡

ዓምድ 4 : -ከተማ፡ -ከከተማው ጥናት የተመረጠው የከተማ ስም በተሰጠው ቦታ በትክክል መሞላቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ ኮዱ ደግሞ በካርድ ኮለሞች ይሞላል፡፡

ዓምድ 5፡ -ክፍተኛ/ ወረዳ/፡ - ጥናቱ በከተማ የተካሄደ ስለሆነ የከፍተኛው/የወረዳው ስም ፣በዓምዱ በተሰጠው ቦታ መሞላቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

ዓምድ 6፡ - ቀበሌ፡ - በከተማው ውስጥ ቀበሌው የሚጠራበት ስም/ቁጥር በተሰጠው ቦታ መሞላቱን ማረጋገጥ እና በካርድ ኮለሞቹ ደግሞ የቀበሌው ኮድ ከአካባቢው መለያ ኮድ በመጠቀም ይሞላል፡፡

ዓምድ 7፡ -የቆጠራ ቦታ፡-የቆጠራ ቦታ ኮድ በካርድ ኮለሞቹ በትክክል መሞላቱን ማጤን ያስፈልጋል፡፡

ዓምድ 8፡ - የተመረጠው ቤተሰብ የምርጫ ተራ ቁጥር፡- በአንድ የቆጠራ ቦታ በጥናቱ የሚመረጡ ቤተሰቦች በጠቅላላ ብዛት 30 ነው፡፡ ስለሆነም በዚህ ዓምድ ባሉት በካርድ ኮለም የተሞሉት ቁጥሮች ከ01-30 መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

ዓምድ8ሀ፡- የቤተሰብ ኃላፊ ሙሉ ስም : - በዚህ ዓምድ የቤተሰቡ ኃላፊ ሙሉ ስም መፃፉን እንዲሁም በክፍል 2 ዓምድ 11 በመጀመሪያ ተራ ቁጥር ላይ መመዝገቡን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ ይህ ባይሆን ግን ከተቆጣጣሪው በሚሰጠው መመሪያ መሠረት ማስተካከል ያስፈልጋል፡፡

ዓምድ 9ሀ፡- ቅ/ጽ/ቤት

በዚህ ዓምድ የቅ/ጽ/ቤቱ ሥም በዓምዱ በተሰጠው ቦታ ተሞልቶ ለቅ/ጽ/ቤቱ የተሰጠው መለያ ኮድ ደግሞ ከዓምዱ ሥር ባሉት ሁለት ካርድ ኮለሞች ይሞላል፡፡

ዓምድ 9ለ፡-የቆጠራ ቦታ ተከታታይ ተራ ቁጥር

ከተዘጋጀው ኮድ መጽሐፍ /Code Book/ ለዚህ ቆጠራ ቦታ የተዘጋጀው ኮድ በሁለቱ ካርድ ኮለሞች ይሞላል፡፡

ዓምድ 9ሐ፡-የቀጠለ መጠይቅ አለ?

ከተሞላው መጠይቅ በተጨማሪ የቀጠለ ወይም የተጨመረ መጠይቅ መኖሩንና አለመኖሩን የሚረጋገጥበት ስለሆነ መጠይቁ ታርሞ ከማለቁ በፊት በጥንቃቄ መታየት ይኖርበታል፡፡ የተሞላውን ኮድ ምልክት መሠረት በማድረግ የቀጠለ አለመኖሩን ማጣራትና ተገቢውን እርማት ማድረግ ተገቢ ነው፡፡ የቀጠለ መጠይቅ ካለ ከዋናው መጠይቅ ጋር በስቴፕለር መያያዝ ይኖርበታል፡፡

## ክፍል 2፡- ስለቤተሰብ አባላት ዝርዝር መረጃ

## ከዓምድ 10-14 ለሁሉም የቤተሰብ አባላት የሚጠየቁ ጥያቄዎች

ዓምድ 10፡- ተራ ቁጥር፡-ይህ ከ01 በመጀመር በተከታታይ ቁጥር የተሰጠበት ስለሆነ ምንም አይነካም፡፡ ሆኖም የቤተሰቡ አባላት ከ11 በላይ በመሆናቸው በተጨማሪነት ጥቅም ላይ የዋለ መጠይቅ መኖሩ ከተረጋገጠ ወይም በእያንዳንዱ መጠይቅ የቀኝ አናት ላይ የቀጠለ መጠይቅ አለ በሚለው አንፃር ኮድ 1 ከተሞላና ተራ ቁጥሮቹ በመስክ ላይ ካልተስተካከሉ አራሚው በተጨማሪው መጠይቅ ላይ "01"ን ወደ "12"፣ "02" ን ወደ "13" ...ወዘተ. በመቀየር ማረም ይኖርበታል፡፡ 12 አባላት ላሉት ቤተሰብ የ12ኛው አባል መረጃ ሌላ መጠይቅ ሳያስፈልግ

እዛው መጠይቅ ግርጌ ከ11ኛው አባል በመቀጠል ሊሞላ ስለሚችል አራሚዎች በሥራቸው ወቅት ይህን ማስተዋል አለባቸው::

ዓምድ 11: -የቤተሰብ መደበኛ አባላት ሙሉ ስም: - የቤተሰቡ አባላት ስም የሰፈረበት ዓምድ ስለሆነ ምንም ዓይነት እርማት አይደረግበትም::

ዓምድ 12: -ከቤተሰቡ ኃላፊ ጋር ያላቸው ዝምድና:-በዚህ ዓምድ ስር ባለው ንዑስ ዓምድ መረጃ ሰብሳቢው መሙላት ያለበት የኮድ ቁጥሮች ከ0-8 ያሉትን ብቻ ነው:: አባላቱ ከቤተሰቡ ኃላፊ ጋር ያላቸውን ዝምድና ሲገለፅ የተሰጠው መግለጫና ኮድ ትክክል መሆኑን ማረጋገጥ እና የማይዛመድ ከሆነ ኮዱን ማስተካከል ያስፈልጋል:: የኮዶቹ ዝርዝርና መግለጫቸው ከጥያቄው ሥር ይገኛል::

ዓምድ 13: -ጾታ:-በዚህ ዓምድ በካርድ ኮለሙ መታየት ያለባቸው ኮድ 1 ወይም 2 ብቻ ናቸው:: ስለ ኮዱ ትክክለኛነት በዓምዱ ሥር በተሰጠው ቦታ የሰፈረውን የፆታ መለያ ማየት ያስፈልጋል:: ሆኖም መረጃ ሰብሳቢው በስህተት ኮድ ሳይሰጥ ቢቀር ተቆጣጣሪውን በማማከር የግለሰቡን ፆታ ከልዩ ልዩ ሁኔታዎች ጋር በማገናዘብ መሞላት ይኖርበታል:: ፆታ ካልተፃፈ ስም ታይቶ ይሞላል:: ይህም ካልተቻለ መጠይቁ ወደተሰበሰበበት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ስልክ በመደወል በማጣራት ይሞላል:: ከዚህ ሁሉ ሙከራ በኋላ ግን ይሆናል ተብሎ የሚገመተው በግምት ይሞላል እንጂ ኮድ 9 መሙላት አይፈቀድም::

ዓምድ 14: -ዕድሜ:- ይህ ዓምድ ሁሉም መደበኛ የቤተሰቡ አባላት ተጠይቀው ተሞልቶ የመጣ ነው:: ሆኖም በዚህ ዓምድ ባሉት ንዑስ ዓምዶች ከ97 በላይ ቁጥር መታየት የለበትም ከ97 በላይ የሆነ ቁጥር ከታየ "97" ተብሎ መስተካከል ይኖርበታል:: ዕድሜ ካልተፃፈ ዝምድናና የልጆች ዕድሜ ፣የባል/የሚስት ዕድሜ ታይቶ በተቀራራቢ እሳቤ/ግምት/ ይሞላል:: በተጨማሪም የዕድሜ መረጃ ካልተሞላ የቤተሰብ አመዘጋገብ ቅደም ተከተልና በዕድሜ ከተሞሉ ዓምዶች ለግለሰቡ የተሞሉ መረጃዎችን በማመሳከር ከተቆጣጣሪው ጋር በመመካከር መረጃዎችን ለመሙላት ይሞክራል እንጂ ኮድ 99 መሞላት የለበትም::

ዓምድ 15-16 :-የትምህርት ሁኔታ /ዕድሜያቸው 5 ዓመትና በላይ ለሆኑ ብቻ/

እነኚህ ዓምዶች የሚሞሉት ዕድሜያቸው 5 ዓመትና በላይ ለሆናቸው ብቻ ስለሆነ ከ5 ዓመት በታች ለሆነ ልጅ መረጃ ተሞልቶ ከመጣ ስህተት ስለሆነ ለሚመለከተው ተቆጣጣሪ በማሳወቅ መረጃውን መሠረዝ ያስፈልጋል:: በአንፃሩም ከ5 ዓመት በላይ የሆነ ግለሰብ መረጃ ሳይሞላለት ከመጣ ለሚመለከተው ሰው /ተቆጣጣሪ/ በማሳየት ተገቢውን ኮድ መሙላት ተገቢ ነው::

ዓምድ 15:- ማንበብና መፃፍ ይችላሉ?

ይህ ዓምድ 5 ዓመትና በላይ የሆናቸው የቤተሰቡ አባላት ማንበብና መፃፍ መቻላቸው ተጠይቆ "አዎን" ለመለሱ ኮድ 1 "የለም" ብለው ለመለሱ ደግሞ ኮድ 2 የተሞላበት ነው::ስለዚህ በካርድ ኮለሙ ውስጥ ተሞልተው የሚመጡ ቁጥሮች ከ "1" ወይም ከ "2" ውጭ መሆን የለባቸውም:: ይህ ዓምድ ሳይሞላ ከመጣ በሚቀጥለው ዓምድ /ዓምድ 16/ ላይ ከተሞላው መረጃ ጋር በማገናዘብ ማስተካከል እንደሚቻል መረዳት ያስፈልጋል::


\\Csa02\Survey\continious Labour force Urban round 1\Metadata\Urban Round 2-2003\Manual\Editing & Coding Manual.doc

ዓምድ 16- የጨረሱት ከፍተኛ ክፍል ስንተኛ ነው?

በመጀመሪያ በዚህ ዓምድ መረጃ የሚሞላው በዓምድ 15 ኮድ 1 ለተሞላላቸው ማለትም ማንበብና መጻፍ ለሚችሉ ግለሰቦች ብቻ ስለሆነ በዓምድ 15 ኮድ 2 ለተሞላላቸው በዚህ ዓምድ ምንም ዓይነት መረጃ እንዳልተሞላ ማረጋገጥ ይገባል:: ተሞልቶም ከመጣ ከሚመለከተው ተቆጣጣሪ ጋር በመመካከር መረጃውን መሠረዝ እንደሚያስፈልግ መገንዘብ ያስፈልጋል:: ቀጥሎም ከላይ ባለው ሰፋ ባለ ክፍት ቦታ የተጻፈው መረጃ ከሥር በካርድ ኮለሙ ውስጥ ከተፃፈው ኮድ ጋር መጣጣማቸውን ማገናዘብ ተገቢ ነው:: የኮዱ ዝርዝር በዕዝል 1 ተያይዞ ቀርቧል::

ዓምድ 17-19:- የስልጠና ሁኔታ ዕድሜያቸው 10 ዓመትና በላይ ለሆኑ ብቻ

ከዚህ ዓምድ በኋላ ያሉት ተከታታይ ዓምዶች የሚመለከታቸው ዕድሜያቸው 10 ዓመትና በላይ ለሆኑ ግለሰቦች ብቻ ስለሆነ ከ10 ዓመት በታች ለሆነው የቤተሰብ አባል መረጃ ተሞልቶ አለመምጣቱንና በስህተት ተሞልቶም ከመጣ ለሚመለከተው ተቆጣጣሪ አሳይቶ መረጃውን መሰረዝ ያስፈልጋል:: በአንፃሩም ከ10 ዓመት በላይ ለሆነው ግለሰብ መረጃ ተሞልቶ መምጣት ሲገባው ሳይሞላ ከመጣ ለተቆጣጣሪ ማሳየትና ተገቢው ኮድ እንዲሞላ ማድረግ ያሻል::

ዓምድ 17: - የሙያ የቴክኒክ ስልጠና ወስደው ያውቃሉ?

/ይህ ዓምድ በማንኛውም ስልጠና ዓይነት የምስክር ወረቀት፣ዲኘሎማ፣ዲግሪና በላይ ያላቸውን ይመለከታል::/

በዚህ ዓምድ ለሚገኘው ካርድ ኮለም አዎን ለመለሱ ኮድ 1፣ የለም ለመለሱ ደግሞ ኮድ 2 መሞላቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: በተጨማሪም በዚህ ዓምድ የለም መልሰው ኮድ 2 የተሞላላቸው የሚቀጥሉት ዓምዶች ማለትም ዓምድ 18 እና 19 ሳይሞላላቸው በሰረዝ ታልፈው ወደ ዓምድ 20 መሸጋገራቸውን ማረጋገጥ ተገቢ ነው:: ይህ ዓምድ ሳይሞላ ከመጣ በዓምድ 16 ላይ ከተሞላው መረጃ ጋር በማገናዘብ መሙላት ይቻላል:: ይህም ሲደግ ተቆጣጣሪው ማየት አለበት::

ዓምድ 18:- የሰለጠኑበት የሙያ /ቴክኒክ ሥልጠና/ ዓይነት ምንድን ነው?

በዓምድ 17 የሙያ /የቴክኒካል/ ሥልጠና ወስጄና አጠናቅቄ የምስክር ወረቀት ወይም ከዚያ በላይ አግኝቼአለሁ ብለው መልሰው ኮድ 1 የተሞላላቸው በዚህ ዓምድ የሰለጠኑበት የሙያ (ቴክኒክ ስልጠና ) ዓይነትና ተገቢው ኮድ በካርድ ኮለሙ መሞላቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: የሙያ አይነቶችንና ተገቢው ኮድ በካርድ ኮለሙ መሞላቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: የሙያ አይነቶችን ከተገቢው ኮድ ጋር ለማገናዘብ ከታች የቀረበውን ዝርዝር ይመልከቱ::

## (ሀ) ፕሮፌሽናልና፣ መለስተኛ ፕሮፌሽናል፣

01 ግብርና ሳይንስ
እርሻ ኢኮኖሚክስ፣እርሻ ምህንድስና፣እርሻ ኤክስቴንሽን ፣ የእንስሳት ሳይን የስኬል ጥበቃ፣ አጠቃላይ እርሻ፣የደረቅ አካባቢ እፅዋትየእንስሳት፣ ግጦሽ ሳይንስ፣ ፖስት ሃርቨስት ቴክኖሎጃ፣. የእንስሳት ፕሮዳክሽንና

02 ውሀና አፈር ጥበቃ፣

03 ደን ሳይንስ፣

04 አጠቃላይ ሕክምና
አፕቶሞሎጂ፣ፓቶሎጂ፣ኢንተርሽናል ሜድስን ፣ጋይናኮሎጂ፣ሰርጀሪ ፣ኢንስቲቲዮሎጂ፣

05 ሜዲካል ላብራቶሪ/ራዲዬሎጂ/

06 ፋርማሲ/ፋርማሲ ቴክኒሽያን/

07 ሳኒተር ሳይንስ

08 ክሊኒካል ሳይንስ/ነርሲንግ

09 ፓብሊክ ሄልዝ ነርስ ጤና መኮንን፣የአካባበ ጤና ፣ ፓስት ሄልዝ ኦፊሰር

10 ፐርሶኔልና ቢዝነስ ማኔጅመንት

11 ኢኮኖሚክስ

12 ሂሣብ አያያዝ /ACCOUNTING/

13 ሴክሬቴሪያል ሳይንስ

14 ባንክና ፋይናንስ

15 ሕግ

16 ስነጽሑፍና ቋንቋ የኢትዮጵያ የውጭ ቋንቋዎች ስነፅሑፍ/

17 ሥነኪነት

18 ኢዱኬሽን ፔዳጎጂ
መምህርነት፣ካሪኩለም ኢንስትራክሽን፣ ኢዱኬሽን አድሚኒስትሬሽን ፣ የጐልማሶች ትምህርት

19 ጂኦግራፊ

20 ታሪክ

21 ፖለቲካል ሳይንስ

22 ሶሲዮሎጂዎና አንትፖሎጂ

23 ስነልቦና /ሳይኮሎጂ/

24 ሲቪል መሃንዲስ/ህንፃ መሃንዲስ/

25 መካኒካል መሃንዲስ

26 ኤሌክትሪካል መሃንዲስ

27 ኢንዱስትሪያል ምህንድስና

28 የማዘጋጃ ቤት ምህንድስና/አርክቴክቸር

38 ባዮሎጂ (ስነሕይወት)

39 ኬሚስትሪ

40 ጂኦሎጂ

41 ፊዚክስ

42 ማቲማቲክስ

43 ስታቲስቲክስ

44 ዲሞግራፊ

45 የኮምፒውተር ሳይንስ/ኢንፎርሜሽን ሳይንስ

46 ጤናና የአካል ማሰልጠኛ ትምህርት

## (ለ) የሙያና ቴክኒክ፣

47 የባልትና ሳይንስ

48 የቆዳ ሥራዎች ሥልጠና

49 የውበት ሥራዎች ሥልጠና

50 የቪድዮ ፎቶግራፍ ቀረጻ ሥልጠና

51 ሸክላ ስራ

52 ሽመና

53 እንጨት ሥራ /የአናጢነት ስልጠናን ይጨምራል/

54 ኤሌክትሪክ ሥራ

55 ብረታ ብረት ብየዳና ቅጥቀጣ

56 መካኒክ /የመኪና/ የሞተር ሳይክል/ የአውሮፐላን ጥገናን ይጨምራል/

57 ግንበኝነት

58 ታይፐ

59 ልብስ ስፌት

60 ሹፌርነት

61 የልማት ተጠሪ /DA/

62 ልምድ አዋላጅ

63 ኮምፒውተር አጠቃቀም

64 በግብርና አነስተኛ ስልጠና ሙያ /ከአጋርፋ፣ አርዳይታ፣ ባኮ፣

65 ሆቴልና ቱሪዝም


\\Csa02\Survey\continious Labour force Urban round 1\Metadata\Urban Round 2-2003\Manual\Editing & Coding Manual.doc

| | | | |
|---|---|---|---|
| 29 | ለሎች ምህንድስናዎች<br>ድራይላንድ ባዮዲይቨርስቲ፣<br>ሃይድሮሊክስ ፣<br>የመስኖ ምህንድስና | 66 | ፖሊስ |
| 30 | አውቶሞቲቭ ቴክኖሎጂ | 67 | ውትድርና |
| 31 | ኮንስተራክሽን ቴክኖሎጂ | 68 | ሌላ ፕሮፌሽናልና፣ መለስተኛ ፕሮፌሽናል /ይገለጽ/ |
| 32 | ድራፍቲንግ ቴክኖሎጂ | 69 | ሌላ የሙያና ቴክኒክል /ይገለጽ/ |
| 33 | ማኒፋክቸሪንግ ቴክኖሎጂ | | |
| 34 | የብረታ ብረት ቴክኖሎጂ | | |
| 35 | የእንስሳት ጤና አጠባበቅ (የከብት ሕክምና/ | | |
| 36 | ኮሙኒኬሽን | | |
| 37 | ፓወርና የመሳሰሉት<br>ኢንስትሩመንቴሽን ፣<br>ኤሌክትሪካል ፓወር፣ ሜካኒካል ፓወር፣<br>ማኒፋክቸሪንግ ፓወር፣ | | |

*ዓምድ 19፡-* ***በሠለጠኑበት ሙያ/መስክ ሥራ ይሠራሉን? ካልሠሩ ለምን?***

በዚህ ዓምድ የሚጠየቁት ግለሰቦች የሙያ ስልጠና ወስደውና በዓምድ 17 " አዎን" ብለው የመለሱ ሲሆን፣ በዚህ ጥያቄ ደግሞ ቢያንስ ካሁን በፊት በሰለጠኑበት በማናቸውም ሙያ አሁን እየሰሩ እንደሆነና እንዳልሆነ ተጠይቀዋል:: ስለሆነም እየሰሩ ከሆነ ኮድ "00" ተሞልቶ "እየሰራሁ" ነው የሚል ደግሞ መፃፉን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: በሌላ ሁኔታ ላይ ላሉ ደግሞ ከተሰጡት አማራጭ መልሶችና ተገቢው ኮድ መሞላቱንና ይህም ከ01-11 ባለው ውስጥ መሆኑን ማረጋገጥ ይገባል::

*ዓምድ 20፡-* ***የጋብቻ ሁኔታ፡-***

ይህ ዓምድ የሚሞላው ዕድሜያቸወ 10 ዓመትና በላይ ለሆናቸው የቤተሰብ አባላት ብቻ ስለሆነ ከ10 ዓመት በታች ለሆኑ ግለሰቦች ሳይሞላ መምጣቱን በስህተት ተሞልቶም ከመጣ ከተቆጣጣሪው ጋር በመመካከር መረጃውን መሰረዝ ያስፈልጋል:: በአንፃሩም ከ10 ዓመት በላይ ለሆነው ግለሰብ መረጃ ተሞልቶ መምጣት ሲገባው ሳይሞላ ከመጣ አስፈላጊውን እርምት/ማገናዘብ በማድረግ ኮድ መሞላት ይኖርበታል:: በተጨማሪም በካርድ ኮለም ውስጥ ተሞልተው የመጡ ቁጥሮች ከኮድ 1-5 ከተዘረዘሩት ውጭ እንዳልሆኑ ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

## ክፍል 3፡- *ያለፉት 6 ወራት የሥራ ሁኔታ*

## ከዓምድ 21-26 / ዕድሜያቸው 10 ዓመትና በላይ ለሆናቸው ብቻ/

*ዓምድ 21፡-* ***ባለፉት 6 ወራት ለጥቂት ጊዜም እንኳን ቢሆን በምርታማ ሥራ ማለትም ተቀጥረው ወይም ትርፍ ለማግኘት ወይም ለቤተሰብዎ ገቢ በሚያስገኝ ሥራ ተሰማርተው ነበር ?***

ለዚህ ጥያቄ እንደ አማራጭ የተሰጡት መልሶች "አዎን" እና "የለም" ሲሆኑ በዚህ መሠረት በዓምዱ ስር "አዎን" የሚለው ቃል ከተፃፈ በካርድ ኮለሙ

ኮድ 1 መፃፉን ማገናዘብ ያስፈልጋል:: ይህ ሁሉ ከተረጋገጠ በኋላ "አዎን" ብለው ኮድ 1 የተሞላላቸው ቀጣዩን ዓምድ ሳይጠየቁ ወደ ዓምድ 23 መተላለፋቸውን ማረጋገጥ ተገቢ ይሆናል::

ዓምድ 22:- <u>ባለፉት 6 ወራት ውስጥ ለጥቂት ጊዜም ቢሆን ሥራ ለማግኘት /ለመሥራት ዝግጁ ነበሩ ?</u>

ለዚህ ጥያቄ መልስ ሰጪዎች በዓምድ 21 ኮድ "2" የተሞላላቸው ሲሆኑ፣ ይህን ዓምድ ደግሞ ከተሰጡት አማራጭ መልሶች ውስጥ አንዱን ማለትም አዎን ኮድ "1" ወይም የለም ኮድ "2" ሊሞላላቸው ይገባል:: የለም ብለው መልሰው ኮድ "2" የተሞላላቸው ቀጣይ ዓምዶችን /ከ23-25/ ሳይሞላ ወደ ዓምድ 26 መተላለፋቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

<u>ዓምድ 23:-</u> <u>በ ----- ወር ለምን ያህል ሳምንታት በምርታማ ሥራ ላይ ተሰማርተው ነበር ወይም ደግሞ ለምን ያህል ሳምንት ሥራ አጥ ነበሩ ?</u>

ይህ ጥያቄ ተጠያቂዎች ባለፉት 6 ወራት ምን ያህል ሳምንታት በሥራ ላይ ምን ያህል ደግሞ ሥራ አጥ እንደነበሩ ለማወቅ በወራት ተከፋፍሎ ተጠይቋል:: በዚህም መሠረት በእያንዳንዱ በዓምድ /Column/ የወር ስም የተፃፈ ሲሆን፣ የሥራ ሁኔታ ተብሎ "ሥራ ላይ" እና "ሥራ አጥ" ተብሎ አግድም/Row/ ተሞልቷል:: ስለሆነም በእያንዳንዱ ወር አንፃር "ሥራ ላይ" የሚለው እና "ሥራ አጥ" የሚለው ድምር ከ4 /ሣምንት/ መብለጥ አይኖርበትም /የነሐሴ ወር ብቻ 5 ሊሆን ይችላል/:: በተመሣሣይ ሁኔታም "ሥራ ላይ" በሚለው ትይዩ የተሞሉት የሳምንታት ብዛት ድምር በሚለው አቅጣጫ ሲታይ ከ25 መብለጥ የለበትም:: በመጨረሻም ጠቅላላ ድምር/ጠ/ድምር/ በሚለው አንፃር ሊሞላ የሚችለው ትልቁ ቁጥርም 25 ስለሆነ የተሞላው ከዚህ ያልበለጠ መሆኑን ማስተዋል ይገባል:: በዓምድ 21 ኮድ 1 ለተሞላላቸው ምርታማ ሥራ ለሰሩ በዓምድ 23 "ሥራ ላይ" በሚለው አግድም/Row/ ቢያንስ በአንዱ ወር ላይ የተመዘገበ የሣምንታት ብዛት መኖሩን ማረጋገጥ ይገባል:: በአንፃሩም በዓምድ 22 ኮድ 1 የተሞላላቸው ለሥራ ዝግጁ ነኝ ላሉት በዚሁ ዓምድ ላይ "ሥራ አጥ" በሚለው አግድም/Row/ ቢያንስ በአንዱ ወር የተሞላ የሳምንታት ብዛት መኖር አለበት::

<u>ዓምድ 24:-</u> <u>ሥራ ሳይኖርዎት ቆይተው ባለፉት 6 ወራት የጀመሩት ሥራ ነበርን?</u>

ይህ ዓምድ ከላይ /በዓምድ 21 ኮድ 1 ለተሞላላቸው በሙሉ የሚያስተናግድ ሲሆን፣ መጠየቅ የማይገባቸው ደግሞ አለመጠየቃቸውን ማጣራት ያስፈልጋል:: ለምሳሌ በዓምድ 22 ኮድ 1 የተሞላላቸው ለመሥራት ዝግጁ የነበሩበት ሳምንታት ብዛት በዓምድ 23 "ሥራ አጥ" በሚለው አግድም/Row/ አንፃር የተሞላላቸው ሲሆን እነዚህ ሥራ አጦች ይህ ጥያቄ አለመጠየቃቸው ማረጋገጥ ያስፈልጋል፣ ከተጠየቁም የሰጡት መልስ መሰረዝ አለበት:: ለዚህ ጥያቄ ኮድ "1" አዎን ኮድ "2" "የለም" የሚሉ አማራጮች የተሰጠ ሲሆን፣ መረጃ ሰብሳቢው ከተሰጡት ኮዶች ውጭ አለመመላቱን ማረጋገጥ ይገባል::

<u>ዓምድ 25:-</u> <u>ባለፉት 6 ወራት ሥራ ላይ /ሥራ አጥ የነበሩበት አጠቃላይ የሳምንታት ድምር ፣</u>

በዓምድ 23 የመጨረሻው ንዑስ ዓምድ ማለትም ጠ/ድ የሚለውን በማየት የተሞላ ሲሆን ይህም የማጣሪያ ዓምድ ነው:: ይህም ማለት በዓምድ 23 ጠ/ድ

በሚለው አንፃር 13 ሳምንታት በታች የተሞላ ከሆነ በዚህ ዓምድ ኮድ 1 የሚሞላለት ሲሆን፣ ከ13 ሳምንታት እና በላይ ከሆነ ደግሞ ኮድ 2 ተሞልቷል:: ይህ ሳይሆን ቀርቶ ከሆነ ግን ወደ ኋላ ሄዶ ዓምድ 23ትን በመመልከት በተሰጠው መመሪያ መሠረት ማስተካከል ይገባል:: በተጨማሪም በዚህ የማጣሪያ ጥያቄ ኮድ 2 የተሞላላቸው ቀጣዩን ዓምድ 26 ሳይጠየቁ ወደ ዓምድ 27 መሸጋገራቸውን ማጣራት ያሻል::

<u>ዓምድ 26</u>:- <u>ባለፉት 6 ወራት ከ13 ሳምንታት በላይ ሥራ ያልሰሩበት ወይም/ሥራ ለመስራት ዝግጁ ያልነበሩበት ምክንያት ምን ነበር?</u>

ይህ ዓምድ ለመልስ ሰጪዎች ስራ ያልሰሩበትን ምክንያት ከተሰጡት አማራጮች ከ1-8 የመለሱ ሲሆን ከነዚህ ቁጥሮች/ኮዶች/ ውጭ ሌላ ከተሞላ መስተካከል ያስፈልገዋል:: በመሆኑም ሥራ ያልሠሩበት ዋነኛ ምክንያት በዓምዱ በተሰጠው ክፍት ቦታ ተገልጾ ተገቢው ኮድ ደግሞ ከስር ባለው ካርድ ኮለም ተሞልቶ መምጣቱን ማረጋገጥ ይገባል:: በተጨማሪም በዓምድ 22 የለም ብለው ኮድ "2" እና በዓምድ 25 ኮድ 1 የተሞላላቸው/ ከ13 ሳምንታት በታች ለሠሩት/ ለዚህ ጥያቄ መልስ መስጠታቸው ይረጋገጣል::

## ክፍል 4 - <u>ያለፉት 7 ቀናት የሥራ ሁኔታ</u>

<u>ዓምድ 27</u>:- <u>ባለፉት 7 ቀናት ለጥቂት ጊዜም እንኳን ቢሆን በምርታማ ሥራ ማለትም ተቀጥረው በክፍያ ወይም ትርፍ ለማግኘት ወይም ለቤተሰብዎ ገቢ በሚያስገኝ ሥራ ተሰማርተው ነበር ?</u>

ይህ ጥያቄ ከዚህ በኋላ ለሚመጡ ዓምዶች መነሻና መሠረታዊ ጥያቄ ስለሆነ በጥንቃቄ መሞላቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: ስለሆነም በመጠይቁ ላይ ከተዘረዘሩት ምርታማ ሥራዎች ቢያንስ በአንዱ ለተሰማራ የቤተሰብ አባል "አዎን" የሚለው ኮድ 1 መሞላቱን በአንፃሩም በአንዱም እንኳን ላልተሰማራ "የለም" የሚለው ኮድ 2 መሞላቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: ስለዚህ በካርድ ኮለሞቹ ውስጥ መታየት የሚገባቸው ኮድ 1 ወይም ኮድ 2 ብቻ መሆን አለባቸው:: በተጨማሪም "የለም" መልሰው ኮድ 2 የተሞላላቸው የሚቀጥሉትን ሁለት ዓምዶች (28 እና 29)ን ሳይጠየቁ ወደ ዓምድ 30 መሻገራቸውን ማረጋገጥ ተገቢ ነው::

ዓምድ 28:- <u>የምሣና የጉዞ ሰዓትን ሳይጨምር ባለፉት 7 ቀናት በሥራቸው በሁሉም ሥራዎች ለስንት ሠዓት ሰርተዋል? / የትርፍ ሰዓትንም ሥራ ያጠቃልላል/</u>

በዚህ ዓምድ ባለፉት 7 ቀናት በጠቅላላው የተሰራ የሥራ ሰዓት መጠን መመዝገቢያ ነው:: ይህ ዓምድ የሚመለከታቸው በዓምድ 27 ኮድ 1 የተሞላላቸው ምርታማ ሥራ ለሰሩት ብቻ የተሞላ መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: የሳምንት የሥራ ሰዓትም ድምር "97" እና ከዛ በላይ ከሆነ "የሳምንቱ ድምር" በሚለው ንዑስ ዓምድ ሥር መታየት ያለበት ቁጥር "97"

ብቻ ነው። በተለየ መልክ ተሞልቶ ከተገኘ ዓምዱን ማረምና ማስተካከል ያስፈልጋል። በተቻለ መጠን በነዚህ ዓምዶች <u>ኮድ 99 አለመሞላቱን ማረጋገጥ</u> ያስፈልጋል።

<u>ዓምድ 29</u>:- <u>በዓምድ 27 ባለፉት ሰባት ቀናት የሰሩት የስራ ሰዓት ድምር</u>

ለዚህ ጥያቄ የቀረቡት ሁለት አማራጭ መልሶች ሲሆኑ እነሱም ኮድ "2" 4 ሰዓትና በላይ ሲሆን ኮድ "1" ደግሞ ከ4 ሰዓት በታች የሚሉ ናቸው። በመሠረቱ የዚህ ዓምድ መረጃ መልስ ሰጪዎችን ሳይጠይቁ ዓምድ 28 ላይ የተሞላውን የስራ ሰዓት ድምር በማየት የሚያጣራበት ስለሆነ የማጣራቱ ሥራ በትክክል መካሄዱን ዓምዱ ላይ ከተሞላው ጋር ማገናዘብ ያሻል። በተጨማሪም ለዚህ ዓምድ ኮድ 2 የተሞላላቸው ብቻ ቀጣዩን ዓምድ ሳይጠየቁ ወደ ዓምድ 31 መሸጋገራቸው መረጋገጥ ይኖርበታል።

ዓምድ 30:- <u>ሥራ እያለዎት ነበር ባለፉት 7 ቀናት በሥራ ላይ ያልተሰማሩት?</u>

ይህ ዓምድ መሠረታዊነት ያለውና ከቤተሰብ አባላት መካከል ሥራ ያላቸው የሥራ ግንኙነታቸው፣ እንዲሁም ሥራ አጦችና ከሁለቱም ውጭ የሆኑትን ማለትም በተለያየ ምክንያት ያልሰሩትን ለመለየት ስለሚረዳን ነው። በዚህ ዓምድ መረጃ ተሞልቶ የሚመጣው በዓምድ 27 ኮድ 2 ለተሞላላቸውና በዓምድ 29 ደግሞ ከ4 ሰዓት በታች ሠርተው ኮድ 2 ለተመዘገበላቸው ነው። ስለዚህ ከ4 ሰዓት በታች ለሠሩ የቤተሰብ አባላት ሥራ እያላቸው ባለፉት 7 ቀናት ውስጥ በሥራ ላይ ካልተሰማሩ አዎን የሚለው ኮድ "1-3" ሲሞላ ነገር ግን ሥራ አጥ ለነበሩና በተለያየ ምክንያት ሥራ ላልሰሩ የለም የሚለው ኮድ "4" ሊሞላላቸው ይገባል። በመጨረሻም በዚህ ዓምድ የለም በሚለው ኮድ "4" የተሞላላቸው ግለሰቦች እስከ ዓምድ 42 ድረስ ምንም መረጃ ሳይሞላላቸው በሰረዝ "-" ታልፈው በቀጥታ ወደ ዓምድ 43 መሸጋገራቸውን ማረጋገጥ ይገባል።

ዓምድ 31-33:- የሥራ ዓይነት የድርጅት ዋና ምርት /አገልግሎት የቅጥር ሁኔታ/Employment Status/

<u>ዓምድ 31</u>:- <u>የዋነኛ ሥራዎ ዓይነት ምንድን ነው?</u>

በጥናቱ ሳምንት ሥራ ላይ ለነበሩና ሥራ ኖሯቸወ ነገር ግን በጥናቱ ሳምንት ሥራ ላይ ያልነበሩ ግለሰቦች (በዓምድ 30 ከኮድ 1-3 ለተሞላላቸው) በዚህ ዓምድ የዋነኛ ሥራቸው ዓይነት ተሞልቶ መጥቷል። ለዚህ ዋነኛ የሥራ ዓይነት ተገቢ የሆነው የመለያ ኮድ "የሥራ ዓይነትና የድርጅት ዋና ምርት

ወይም አገልግሎት ምደባና ኮድ ዝርዝር" ተብሎ ከተዘጋጀው መጽሐፍ በመውሰድ ኮዱ የተሞላ ቢሆንም የኤዲተሮች ዋና ሥራ የሚሆነው የኮዱን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ነው:: የዋነኛ የሥራ ዓይነት ከኮድ ዘርዝር መጽሐፍ ውስጥ መጣጣም ካልቻለ ለሚመለከተው ተቆጣጣሪ በማሳየት ቢቻል ተቀራራቢ የሆነውን የሥራ ዓይነት ኮድ መሙላት ያስፈልጋል:: አንዳንድ ጊዜ በመስክ የተሞላው የሥራ ዓይነት ግልፅና በቀላሉ የማይነበብ ለመረዳትም አስቸጋሪ ከሆነ ኢዲተሩ በእርጋታና በትዕግስት መረጃ ሰብሳቢው የሞላውን ማጣራት ይኖርበታል:: ከዚህም በተጨማሪ ከሥራ ዓይነት ኮድ ዝርዝሩ ጋር ለማገናኘት ሲሞክር በቅድሚያ የተጠቀሰው የሥራ ዓይነት በየትኛው ዋና ክፍል እንደሆነ መለየት ከዚያም በዋና ክፍሉ ሥር ከተዘረዘሩት የሥራ ዓይነቶች ለየትኛው እንደሚቀርብ አመዛዝኖ ኮድ ማድረግ ያስፈልጋል:: በሆኑም ለመወሰን አስቸጋሪ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ በመጠራጠር ኮድ ከማድረግ መቆጠብና ተቆጣጣሪውን በማማከር ትክክለኛውን ኮድ መስጠት ይገባል:: ስለዚህ በኮድ ዝርዝሩ ከተሰጠው የማይጣጣም ሆኖ ከተገኘ ከተቆጣጣሪውና ከአሰሪው ክፍል ጋር ተነጋግሮ አዲስ ኮድ መስጠት ሊያስፈልግ ይችላል::

ዓምድ 32:- <u>በዋነኛነት የሚሰሩበት ድርጅት ዋና ምርት ወይም የሚሰጠው አገልግሎት ዓይነት ምንድን ነው?</u>

በተመሳሳይ ሁኔታ በጥናቱ ሳምንት በሥራ ላይ ለነበሩና ሥራ ኖሯቸው በጥናቱ ሳምንት ሥራ ላይ ላልነበሩ ግለሰቦች በዚህ ዓምድ በዋነኝነት የሚሰሩበት ድርጅት ዋና ምርት ወይም የሚሰጠው አገልግሎት ዓይነት /ኢንዱስትሪ/ ተሞልቶ መጥቷል:: ለዚህ የኢንዱስትሪ ዓይነት ተገቢ የሆነው የመለያ ኮድ ከ"<u>የሥራ ዓይነትና የድርጅት ዋና ምርት ወይም አገልግሎት ኮድ ዝርዝር</u>" ተብሎ የተዘጋጀው መጽሐፍ በመውሰድ ኮድ ተሞልቷል::ኤዲተሩ ይህ ትክክል መሆኑን ማረጋገጥ ይጠበቅበታል:: የኢንዱስትሪ ነገር ግን በመስክ ላይ የተሞላው የድርጅት ምርት/አገልግሎት ሳይሆን የድርጅቱ ስም ወይም ሌላ መግለጫ ሊሆን ይችላል:: በዚህን ጊዜ ከተቆጣጣሪው ጋር በመመካከር የድርጅቱ ዋና ምርት/አገልግሎት ምን እንደሆነ ለማወቅ የተለያዩ ግንዛቤዎችንና ሁኔታዎችን በመውሰድ ለመሙላት ይሞከራል::

ዓምድ 33:- <u>የዋነኛ ሥራዎ የቅጥር ሁኔታ(**Employment Status**) ምንድን ነው?</u>

ለዓምዱ የተሰጠው ክፍት ቦታ ተሞልቶ የመጣው የቅጥር ሁኔታ ከሥር በካርድ ኮለሙ ከተሞላው ኮድ ጋር መጣጣሙን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: በተጨማሪም ከጥያቄው ሥር የተዘረዘሩት **11** አማራጭ መልሶች ከኮድ **01-11** ብቻ ስለሆኑ ከነዚህ ቁጥሮች ውጭ ሳይሞላ መምጣቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: እንዲሁም ከኮድ **06-09** የተሞላላቸው ግለሰቦች ተከታዮቹን ዓምዶች ሳይጠየቁ ወደ ዓምድ **39** ማለፋቸውን ማረጋገጥ ሲገባ ኮድ **10** የተሞላላቸው ደግሞ ወደ

ዓምድ 40 መሸጋገራቸውን ማጣራት ተገቢ ይሆናል፡፡ የአማራጭ መልሶች ዝርዝር መጠይቁ ላይ ከጥያቄው ሥር ቀርበዋል፡፡

ዓምድ 34-38 ከቅጥር ሥራ የተገኘ ክፍያ

ዓምድ 34:- ለሥራዎ የሚከፈልዎት በገንዘብ ነው ወይስ በዓይነት?

በዚህ ዓምድ ጥያቄው የተጠየቀላቸው ከላይ በዓምድ 33 ከኮድ 01-05 እንዲሁም ኮድ 11 ለተሞላላቸው ስለሆነ ከነዚህ ኮዶች ውጭ (06-10) የተሞላላቸው ግን ይህንን ዓምድ አለመጠየቃቸውንና ከተጠየቁም በጥንቃቄ ታርሞ ተገቢው ኮድ እንዲሞላላቸው ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም ለዚህ ጥያቄ ለተሰጡት 3 አማራጭ መልሶች የተዘጋጁት 3 ኮዶች በመሆናቸው ከነዚህ ውጭ በተከታታይነት ተሞልተው ከመጡት ሌሎች መረጃዎች ጋር በማገናዘብ ከተቆጣጣሪው ጋር በመሆን ማስተካከል ተገቢ ይሆናል፡፡ አማራጭ መልሶቹ ከጥያቄው ስር ስለተዘረዘሩ የተሞላውን ኮድ ተመሳሳይነትም ማገናዘብ ይገባል፡፡

ዓምድ 35:- ለዋናው ሥራዎ የአከፋፈል ጊዜ እንዴት ነው?

ይህ ጥያቄ ግለሰቦች በዓምድ 33 ከኮድ 01-05 እንዲሁም ኮድ 11 ተሞልቶላቸው ከሆነ ብቻ ነው የሚጠየቁት ስለሆነም እነዚህ ግለሰቦች ብቻ መጠየቃቸው መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ ለዚህ ጥያቄ ለተሰጡት ሰባት አማራጭ መልሶች ከ1-7 ኮድ ተሰጥቶአቸው ከጥያቄው ስር ተዘርዝረዋል፡፡ ስለሆነም፣ በዓምዱ ስር በጽሁፍ የተገለፀው የአከፋፈል ጊዜና በካርድ ኮለሙ የተሞላው ኮድ መጣጣማቸው ይረጋገጣል፡፡ በመጨረሻም ከኮድ 5-7 የተሞላላቸው ቀጣዮቹን /ሁለት ጥያቄዎች ሳይጠየቁ ወደ ዓምድ 38 ማለፋቸውን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

ዓምድ 36:- በገለፁልኝ አከፋፈል መሠረት ባለፈው ወር ለስንት የአከፋፈል ጊዜያት ሠርተዋል?

በዚህ ጥያቄ ግለሰቦች በዓምድ 33 ከኮድ 01-05 እንዲሁም ኮድ 11 የተሞላላቸው ብቻ መጠየቃቸው ይረጋገጣል፡፡ ጥያቄው በዓምድ 35 በተገለፀው የአከፋፈል ጊዜ መሠረት ለምን ያህል ጊዜ እየተከፈላቸው መሥራታቸውን ተጠይቀው ተሞልቷል በዚህ መሠረት በዓምዱ ሦስት ካርድ ኮለም ተሰጥቷል፡፡ ስለሆነም በዓምድ 35 በየቀኑ ብለው ኮድ "2" የመለሱ በዓምድ 36 ላይ ከ30፣ በየሳምንቱ ኮድ "3" ለተሞላለት ደግሞ ከ4 እንዲሁም በየ15 ቀኑ ብሎ ኮድ "4" ለተሞላላት ከ2 አለመብለጡን በአትኩሮት ማየት ያስፈልጋል፡፡

ዓምድ 37:- በገለፁልኝ አከፋፈል መሠረት ለመጨረሻ ጊዜ ምን ያህል ተከፈልዎት?

ይህ ጥያቄ ግለሰቦች በዓምድ 35 ለገለፁት የአከፋፈል ሁኔታ በመጨረሻው ክፍያቸው ያገኙት የብር መጠን ተሞልቶ መጥቷል:: ለዚህም አራት ካርድ ኮለሞች የተዘጋጁ ስለሆነ በዚሁ መፃፊያ በተዘጋጁት ካርድ ኮለሞች ቁጥሮች ከቀኝ ወደ ግራ መሞላቱን ማረጋገጥ ወሳኝ ነው:: ይህም ማለት የብሩ መጠን በካርድ ኮለሙ ሲፃፍ መጀመር የሚኖርበት ከቀኝ ይሆናል:: ስለዚህ "30 ብር" ያለ መልስ ሰጪ ብሩ በዓምዱ ሲሰፍር "0" "0" "3" "0" መሆን ይኖርበታል:: እዚህ ላይ ከብር "9997" እና በላይ ለሚከፈላቸው "9997" ብቻ መሞላት ይኖርበታል::

ዓምድ 38:- በዋነኛነት ለሠሩት ሥራ ባለፈው አንድ ወር ውስጥ በጠቅላላው ምን ያህል ተከፈልዎት? ይህ ጥያቄ የመልስ ሰጪዎቹ ከቅጥር ሥራ የተገኘ

የወር ክፍያ መጠን የተጠየቀበት ሲሆን በዓምድ 37 ከተሞላው ጋር ሊነፃፀር ይችላል:: ይኸውም የአከፋፈል ጊዜው በሣምንት/አስራ አምስት ቀን የሆነ ሠራተኛ/ቅጥረኛ በዓምድ 37 ያስመዘገበው የገንዘብ መጠን ከዓምድ 38 ማነስ ወይም እኩል መሆን ይጠበቅበታል:: ነገር ግን በተመሳሳይ መልኩም በካርድ ኮለሙ ውስጥ የቁጥሮቹ አፃፃፍ ከላይ በተገለፀው መሠረት ከቀኝ በመጀመር ይሆናል:: የወር ገቢያቸው ከብር "9997" እና በላይ ለሆነ የሚፃፈው ይኸው "9997" ይሆናል::

ዓምድ 39:- ድርጅቱ/የሥራ መስኩ ከ10 እና በላይ ሠራተኞች አሉት ? ወይም የሂሳብ መዝገብ አለው? ወይም ፈቃድ አለው?

መልስ ሰጪዎች ስለሚሰሩበት ድርጅት የሂሳብ መዝገብ/የፈቃድ ሁኔታ ከ10 በላይ የሆነ ተቀጥሮ የሚሰሩ ሠራተኞች እንዳለውና እንደሌለው ተጠይቀዋል:: ለዚህም ጥያቄ ኮድ 1-3 ብቻ የተሰጠ ሲሆን፣ ከነዚህ ኮዶች ውጭ ሌላ አለመሞላቱ መረጋገጥ ይኖርበታል:: በዚህ ጥያቄ በዓምድ 33 ኮድ 03 ከ06-09 እና 11 የተሞላላቸው ግለሰቦች መጠየቃቸው መረጋገጥ ይኖርበታል:: በተለይም በዓምድ 33 ኮድ 03 እና 11 የይለፍ ምልክት ስለሌላቸው በዚህ ዓምድ ሳይዘለሉ መጠየቃቸው ማገናዘብ ያስፈልጋል::

ዓምድ 40:- አብዛኛውን ጊዜ በሳምንት ለስንት ሰዓት ይሠራሉ?

በዚህ ጥያቄ ግለሰቦች አብዛኛውን ጊዜ በተለምዶ/በአማካኝ በሳምንት ውስጥ የሚሰሩት የስራ ሰዓት ተጠይቆ ተሞልቷል:: ስለሆነም አንድ ሰው ሊሞላለት የሚችለው ከፍተኛ የሳምንት የሥራ ሰዓት ብዛት 97 ነው:: ስለሆነም ከዚህ ቁጥር በላይ በካርድ ኮለሙ መታየት አይኖርበትም:: ይህ ጥያቄ በዓምድ 27 ኮድ 1 ለተሞላላቸው ምርታማ ሥራ ለሰሩና፣ ሥራ እያላቸው ባለፉት ሳምንት ስራ ያልሰሩትን ማለትም በዓምድ 30 ከኮድ 1-3 የተሞላላቸው የሚመለከት ስለሆነ

ይህ ጥያቄ መጠየቃቸውን ማረጋገጥ ተገቢ ነው። በተጨማሪም በዓምድ 33 ኮድ 10 የተሞላላቸው የአምራቾች ህብረት ሥራ ማህበር አባላት ይህን ጥያቄ መጠየቃቸው ይረጋገጣል።

ዓምድ 41-42 <u>ክፊል ሠራተኝነት</u>

<u>ዓምድ 41</u>:- <u>/ሥራ ላይ ለነበሩ/ ባለፈው ሳምንት ተጨማሪ ሰዓት ለመሥራት አቅሙም ፍላጐትም ነበረዎ? /ሥራ ላይ ላልነበሩ ባለፈው ሳምንት ለመስራት አቅምም ፍላጐትም ነበረዎት?</u>

ይህ ጥያቄ በዓምድ 29 ኮድ 2 ለተሞላላቸው እና በዓምድ 30 ከኮድ 1-3 ለተሞላላቸው ሁሉ ይጠየቅላቸዋል።

በተጨማሪም ለጥያቄው የተሰጡት አማራጭ መልሶች አዎን ኮድ 1 እና የለም፣ ኮድ 2 ስለሆኑ ከነዚህ ቁጥሮች ውጭ ሌላ አለመሞላቱን መታየት አለበት። በተመሳሳይ መልኩም ኮድ 1 የተሞላላቸው ቀጣዩን ጥያቄ ሲጠየቁ ኮድ 2 የተሞላላቸው ከሆነ ግን ከዚህ በኋላ ምንም ዓይነት ጥያቄ ሳይጠየቁ መረጃ መሙላት ማብቃት ይኖርበታል።

<u>ዓምድ 42</u>: <u>ተጨማሪውን ሰዓት በምን ዓይነት ሥራ ለመሰማራት ይፈልጉ ነበር?</u>

በዓምድ 41 አዎን ብለው ኮድ 1 የተሞላላቸው መልስ ሰጪዎች በዚህም ዓምድ ይህንንም ጥያቄ ተጠይቀዋል። በዓምዱ ደግሞ የተሰጡት አማራጮች ሦስት ስለሆኑ ከኮድ 1-3 ብቻ ኮድ መሙላቱን ማየት ተገቢ ነው። ዝርዝር አማራጭ መልሶቹ ከጥያቄው ስር ስለተገለፁ ከተሞላው ኮድ ጋር መገናዘብ ይኖርበታል። በመጨረሻም ይህንን ዓምድ የተጠየቁ መልስ ሰጪዎች በሙሉ የሚቀጥለው ክፍል ስለማይመለከታቸው የመረጃ መሙላቱ ተግባር ማብቃቱ ይረጋገጣል።

## ክፍል 5

## <u>ሥራ አጥና የሥራ አጥ ባህሪያት</u>

## ከዓምድ 43-52 / ዕድሜያቸው 10 ዓመትና በላይ ለሆናቸው ብቻ/

በዚህ ክፍል መረጃ የሚሰበሰብላቸው ግለሰቦች ባለፉት 7 ቀናት ውስጥ ሥራ ላልሰሩና ሠርተውም በዓምድ 29 ላይ ከ4 ሰዓት በታች ለተመዘገበላቸው ነው። ይህ ማለትም በዓምድ 30 ላይ "የለም" ብለው <u>ኮድ 4 የተሞላላቸውን</u> በሙሉ የሚመለከት መሆኑን በቅድሚያ መረዳቱ ተገቢ ይሆናል።

<u>ዓምድ 43</u>:- <u>ባለፉት 3 ወራት ሥራ ለማግኘት ወይም የግል ሥራ ለመጀመር ጥረት አድርገው ነበርን</u>?

በዚህ ዓምድ የሚጠየቁት ግለሰቦች በዓምድ 30 ላይ ኮድ 4 የተሞላላቸው ናቸው። ከዓምድ 31 ጀምሮ እስከዚህ ዓምድ ድረስ በ----ሰረዝ የታለፈላቸው

መሆኑን ማየትም ያስፈልጋል:: በዓምዱ የቀረቡት አማራጮች "አዎን" ብለው ለመለሱ ኮድ 1 እና "የለም" ላሉ ኮድ 2 ስለሆኑ በተገቢው ካርድ ኮለም ከሁለቱ ኮዶች አንደኛው ብቻ መሞላቱን ማረጋገጥ ይገባል:: ኮድ 2 የተሞላላቸው ቀጣዩን ዓምድ ሳይጠየቁ ወደ ዓምድ 45 መሻጋራቸውን ማየት ያስፈልጋል::

ዓምድ 44:- ሥራ ለማግኘት ወይም ለመጀመር ምን ጥረት አደረጉ?

ግለሰቦች የራሳቸውን ወይም በቅጥር ሥራ ለመጀመር ከሚያደርጉት ሙከራዎች ውስጥ ስምንት አማራጮች ተቀምጠዋል:: ለዚህም በዓምድ 43 ኮድ 1 የተሞላላቸውን ብቻ ይመለከታል:: ስለሆነም ለእነዚህ ግለሰቦች ብቻ የተሞላላቸው መሆኑና በመጠይቁ ግርጌም ከተሰጡት 8 አማራጭ መልሶች አንዱን ከኮድ 1-8 ውጭ አለመሆኑን ማጣራት ይኖርበታል:: ከዚያም ይህንን ጥያቄ የመለሱ በሙሉ ቀጣዩን ዓምድ አለመጠየቃቸውንና ወደ ዓምድ 46 መሻገራቸውን ማጣራት ያስፈልጋል::

ዓምድ 45:- ለምንድን ነው ሥራ ለማግኘት ወይም ለመጀመር ጥረት ያላደረጉት?

በመጀመሪያ ይህ ዓምድ የሚሞላላቸው በዓምድ 43 "የለም" ብለው መልሰው ኮድ 2 ለተሞላላቸው ማለትም ሥራ ለማግኘትም ሆነ ሥራ ለመጀመር ምንም ጥረት ላላደረጉ ግለሰቦች ብቻ ነው:: ሥራ ለመሥራት ወይም ለማግኘት ጥረት ያላደረጉበት ምክንያት በዓምዱ ግርጌ ከተዘረዘሩት 12 አማራጭ መልሶች ውስጥ አንዱ በዓምዱ ሥር መሞላቱንና ተገቢው ኮድ ደግሞ በካርድ ኮለሞቹ መሞላቱን ማረጋገጥ ያሻል:: የተሰጡት ኮዶች ከ01-12 ስለሆኑ በካርድ ኮለሞቹ ተሞልተው የመጡት ቁጥሮችም ከነዚህ ውጭ አለመሆናቸውን ማረጋገጥ ይገባል::

ዓምድ 46:- በሚቀጥለው አንድ ወር ውስጥ ገቢ የሚያስገኝ ሥራ ቢያገኙ ይሠራሉ?

ለዚህ ጥያቄ "አዎን" የመለሱ ግለሰቦች ኮድ 1 "የለም" ብለው ለመለሱ ደግሞ ኮድ 2 እንደተሞላላቸውና በካርድ ኮለሙ ውስጥ መታየት የሚገባቸው ቁጥሮችም ከነዚህ ውጭ እንዳልሆኑ ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: በሌላ በኩል ደግሞ "የለም" ብለው ኮድ 2 የተሞላላቸው ቀጣዩን ዓምድ ሳይጠየቁ ወደ ዓምድ 48 መሻገራቸውን ማጣራት ተገቢ ነው:: በተጨማሪም በዓምድ 44 የተጠየቁት ሁሉ ይህን ጥያቄ መጠየቃቸውን ይረጋገጣል:: በቀን በመደበኛ ትምህርት በመከታተል ላይ ለሚገኙ ተማሪዎች በዓምድ 45 ሥራ ለማግኘት ጥረት ያላደረጉበት ምክንያት ሲጠየቁ "ትምህርት" ብለው ኮድ 05 ከመለሱና በዓምድ 46 ደግሞ ዝግጁ ነኝ ብለው ኮድ 1 ከመለሱ ወደ ኋላ ተመልሶ ዕድሜያቸውን ዓምድ 14፣የጨረሱት ክፍል ዓምድ 16፣ ከ13 ሳምንታት ያልሰሩበት ምክንያት ዓምድ 26ን ጭምር ማገናዘብ እንዲሁም ሌላ የተሰጠ አስተያየት ካለ በማየት መረጃው በትክክል የተሞላ መሆኑን ማረጋገጥ ይገባል::

ዓምድ 47: በአቅምዎ ተቀጥረው ሊሰሩት የሚችሉት ሥራ ቢገኝልዎት ወይም በግል ሥራ ለመሠማራት አስፈላጊ ነገሮች ቢሟሉ ሥራ ለመጀመር ዝግጁ ነዎት ?

በዚህ ዓምድ የሚጠየቁት ግለሰቦች በዓምድ 46 ላይ "አዎን" ብለው መልሰው በሚቀጥለው 1 ወር ሥራ ቢያገኙ ለመስራት ዝግጁ ሆነው /ኮድ 1 የተሞላላቸው/ ናቸው:: ለዚህ ጥያቄ ዝግጁ መሆንና አለመሆናቸው ተጠይቀው ከተሰጡት 2 አማራጮች አንዱ ብቻ መሞላቱን ይረጋገጣል:: ዝግጁ ሆነው ኮድ 2 የተሞላላቸው ደግሞ ቀጣዩን ጥያቄ ሳይጠየቁ ወደ ዓምድ 49 መሻጋገራቸውን ማጣራት ተገቢ ነው

ዓምድ 48:- ለምንድነው ሥራ ቢያገኙ የማይሠሩት?

ይህ ጥያቄ የሚመለከታቸው ዝግጁ እንዳልነበሩ የገለፁ/በዓምድ 47 ኮድ 1 የተሞላላቸውን/ ነው:: ስለሆነም በዚህ ጥያቄ ከተዘረዘሩት ስምንት አማራጭ


\\Csa02\Survey\continious Labour force Urban round 1\Metadata\Urban Round 2-2003\Manual\Editing & Coding Manual.doc

መልሶች መካከል አንዱን ብቻ መምረጣቸውንና ከኮድ 1-8 ብቻ በካርድ ኮለሙ መሞላቱን ማጣራት ያሻል:: በተጨማሪም ይህንን ጥያቄ ከተጠየቁ በኋላ ጥያቄው ማብቃቱ ማየት ተገቢ ነው::

<u>ዓምድ 49</u>:- <u>*የሚፈልጉት ሥራ ምን ዓይነት ነው*</u>?

በዓምድ 47 "ዝግጁ ነኝ" ብለው ኮድ 2 የተሞላላቸው ግለሰቦች በዚህ ጥያቄ ደግሞ ምን ዓይነት ሥራ ለመሥራት እንደሚፈልጉ ተጠይቀዋል:: ለጥያቄው የተሰጡት አምስት አማራጮች ከጥያቄው ስር ተዘርዝረዋል:: ከነዚህ አማራጮች ውስጥ ከኮድ 1-3 የተሞላላቸው ብቻ ቀጣዩን ጥያቄ/ዓምድ ተጠይቀዋል:: ስለሆነም ኮድ 4 እና ኮድ 5 የተሞላላቸው ቀጣዩን ዓምድ ሳይጠየቁ ወደ ዓምድ 51 ማለፋቸውን ማረጋገጥ ይገባል::

<u>ዓምድ 50:-</u> <u>*የግል ሥራ/የራስን ድርጅት ለማቋቋም የገጠሞት/ የሚገጥምዎት ችግር አለ ? ካለ ምንድን ነው?*</u>

ለዚህ ጥያቄ የተሰጡት ዘጠኝ አማራጭ መልሶች ከመጠይቁ ግርጌ የተዘረዘሩት ናቸው:: እነዚህም አማራጮች በዓምድ 49 ከኮድ 1-3 ለተሞላላቸው ግለሰቦች ብቻ ይቀርብላቸዋል:: በዚህ ዓምድ በአብዛኛው የሚያጋጥመው ችግር በዓምድ 49 ላይ ኮድ 4 እና 5 የተሞላላቸውም ይህንን ጥያቄ ተጠይቀው በዚህ ዓምድ ላይ ኮድ 09 "ሌላ" በሚለው ስር ምክንያት ተሞልቶ ይመጣል:: ስለሆነም እንደዚህ ዓይነት ስህተት ሲኖር መታረም ይኖርበታል:: ተሞልተው የመጡት ኮዶች ከ00-09 ካሉት ውጭ አለመሆኑን በጥንቃቄ ማየት ይገባል::

ዓምድ 51:- <u>*ለምን ያህል ወራት ያለሥራ ቆይተዋል*</u>?

በዓምድ 49 የሚፈልጉትን ሥራ ምን ዓይነት እንደሆነ ተጠይቀው "ተቀጥሮ ለመሥራት" ብለው ኮድ 4 ለተሞላላቸውና /ሌላ/ ብለው ለገለፁና ኮድ 5 ለተሞላላቸው እንዲሁም በዓምድ 50 የተጠየቁት በሙሉ ይህንን ጥያቄ ይጠየቃሉ:: በዚህ ዓምድ ሁለት ካርድ ኮለሞች የተሰጡት ሲሆን፣ በክፍት ቦታዎቹም ከኮድ "00" ጀምሮ ተሞልቶ ሊመጣ ይችላል:: በተጨማሪም አንድ አሀዝ/ዲጅት/Digit/ ያለው ቁጥር ከግራ በኩል ባለው ካርድ ኮለም ተጽፎ ከተገኘ በቀኝ በኩል ባለው መጨረሻ ካርድ ኮለም ተሞልቶ መታረም ይኖርበታል:: በካርድ ኮለሙ የተሞላው ቁጥር ከ97 በላይ ከሆነ ተሰርዞ 97 ይደረጋል:: እንደዚሁም በመጀመሪያው ንዑስ ዓምድ ምንም ሳይሞላ በሁለተኛው ንዑስ ዓምድ ብቻ ተሞልቶ ከመጣ የመጀመሪያው ንዑስ ዓምድ ላይ 0 መፃፍ ያስፈልጋል::

<u>ዓምድ 52</u>:- <u>*ከዚህ በፊት በቅጥር ወይም በግል ሥራ ሠርተው ያውቃሉ?*</u>

ለዚህ ጥያቄ "አዎን" ብለው የመለሱ ኮድ 1 "የለም" ብለው ለመለሱ ደግሞ ኮድ 2 ተሞልቶላቸዋል:: ስለሆነም ከሁለቱ አማራጮች ውጭ የተለየ ኮድ ቁጥር አለመሞላቱን ይረጋገጣል::

**<u>አዝል 1</u>**

የጨረሱት ከፍተኛ ክፍል እና ኮዶቻቸው ከዚህ በታች በዝርዝር ቀርቧል፡፡

<u>የጨረሱት ከፍተኛ ክፍል</u>፡-

| <u>ኮድ</u> | <u>በፊደል</u> | <u>የክፍል ደረጃ</u> |
|---|---|---|
| 01. | አንደኛ ትምህርት ተምረው ሳጠናቀቁ | አንደኛ ክፍል |
| 02. | ሁለተኛ ትምህርት ተምረው ሳጠናቀቁ | የሁለተኛ ክፍል |
| 03. | ሶስተኛ ትምህርት ተምረው ሳጠናቀቁ | የሦስተኛ ክፍል |
| 04. | አራተኛ ትምህርት ተምረው ሳጠናቀቁ | የአራተኛ ክፍል |
| 05. | አምስተኛ ክፍል ትምህርት ተምረው ሳጠናቀቁ | የአምስተኛ |
| 06. | ስድስተኛ ትምህርት ተምረው ሳጠናቀቁ | የስድስተኛ ክፍል |
| 07. | ሰባተኛ ትምህርት ተምረው ሳጠናቀቁ | የሰባተኛ ክፍል |
| 08. | ስምንተኛ ትምህርት ተምረው ሳጠናቀቁ | የስምንኛ ክፍል |
| 09. | ዘጠነኛ በአዲሱ፡- የዘጠነኛ ክፍል በአዲሱ ስርዓተ ትምህርት ተምረው ሳጠናቀቁ | |
| 10. | አሥረኛ በአዲሱ፡-የ10ኛ ክፍል በአዲሱ ስርዐተ ትምህርት ተምረው ሳጠናቀቁ፣ ወይም የአሥራ ሁለተኛ ክፍል በቀድሞው ስርዓተ ትምህርት ተምረው ሳጠናቀቁ | |
| 11. | አሥራ አንደኛ/ Preparatory/፡- በአዲሱ ስርዓተ ትምህርት መሠረት የቅድመ ኮሌጅ የቀለም ትምህርት አስራ አንደኛ ክፍልን ተምረው ሳጠናቀቁ | |
| 12. | አስራ ሁለተኛ/ Preparatory/፡- በአዲሱ ስርዓተ ትምህርት መሠረት የቅድመ ኮሌጅ የቀለም ትምህርት አስራ ሁለተኛ ክፍልን ተምረው ሳጠናቀቁ፣ | |
| 13. | ዘጠነኛ በቀድሞ፡- የዘጠነኛ ክፍልበቀድሞው ስርዓተ ትምህርት ተምረው ሳጠናቀቁ፣ | |
| 14. | አስረኛ በቀድሞ፡- የአስረኛ ክፍል በቀድሞው ስርዓተ ትምህርት ተምረውሳጠናቀቁ | |
| 15. | አሥራ አንደኛ በቀድሞ፡- የአሥራ አንደኛ ክፍል በቀድሞው | |

ስርዓተ ትምህርት ተምረው ላጠናቀቁ

16. 10+1/በአዲሱ የሙያ/ :- በአዲሱ ስርዓተ-ትምህርት መሠረት የ10+1 የሙያ ትምህርት ተምረው ላጠናቀቁ፣

17. 10+2/በአዲሱ የሙያ/:-በአዲሱ ስርዓተ ትምህርት መሠረት የ10+2 የሙያ ትምህርት ተምረው ላጠናቀቁ

20:- ሰርተፊኬት:- የ10+1 እና የ10+2 ሥልጠና ኘሮግራሞች ከመጀመራቸው በፊት ከ12ኛ ክፍል በላይ ከመደበኛ ትምህርት ቤቶች ወይም በከፍተኛ ትምህርት መስጫ ከታወቁ ተቋሞች /ኮሌጆች/ ዩኒቨርስቲዎች ወይም ከተመሳሳይ ትምህርት መስጫ ተቋም ዲኘሎም ወይም ዲግሪ ለማስገኘት ባልታቀደ ኘሮግራም ቢያንስ የአንድ ዓመትና ከዚያ በላይ ትምህርት ለፈፀሙና ሁሉ ሰርተፊኬት ለተቀበሉ ሁሉ በዚህ ኮድ ይጠቃለላሉ:: ከታች በማስታወሻ 1 እና በገጽ 63 ዕዝል 2 ከተዘረዘሩት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ውጭ የተከታተሉት ትምህርት ወይም ያገኙት ዕዝል 2 ሰርተፊኬት በዚህ ዓምድ ኮድ 20 ይመዘገባል::

21 ዲፕሎም ወይም 10ቲ3 ያልጨረሱ፣ አሥራ ሁለተኛ ክፍል ትምህርት በላይ በከፍተኛ ትምህርት መስጫ ከታወቀ ተቋም ወይም ኮሌጅ ወይም ዩኒቨርስቲ ወይም ከተመሳሳይ ትምህርት መስጫ ተቋም ዲፕሎም ለማስገኘት በታቀደ የትምህርት ፕሮግራም የአንድ ዓመትና ከዚያ በላይ ትምህርት ያጠናቀቁ ግን ዲፕሎም ላላገኙ ሁሉ::

22 ዲግሪ ያልጨረሱ፣ ከአሥራ ሁለተኛ ክፍል ትምህርት በላይ የመጀመሪያ ዲግሪ /ቢ.ኤ፣ቢ.ኤስ.ሲ/ያስገኛል ተብሎ በታቀደ የትምህርት ኘሮግራም በኮሌጅ ወይም በዩኒቨርስቲ የአንድ ዓመት ወይም የበለጠ ትምህርት ላጠናቀቁ ግን ዲግሪ ላላገኙ ሁሉ፣ የኮሌጆች ፣ የዩኑቨርስቲዎች ዝርዝር በማስታወሻ 1 እና በዕዝል 2 ይገኛል::

23 ዲኘሎም /10+3/ ፣ በከፍተኛ ትምህርት መስጫ ተቋም /ኮሌጅ/ዩኒቨርስቲ ወይም ተመሳሳይ ትምህርት መስጫ ተቋም / ማለትም ማስታወሻ 1 እና በዕዝል 2 ከተዘረዘሩት ከፍተኛ የትምህርት ተቋም ውስጥ ዲፕሎም ላገኙና ተመሳሳይ የትምህርት ደረጃ ላላቸው ሁሉ፣

24 ዲግሪ ፣ የመጀመሪያ ዲግሪ /የሕክምና ዲግሪ፣ ቢ.ኤ፣ ቢ.ኤስ.ሲ፣ ቢ.ኢ.ዲ፣ ኤል.ኤል.ቢ/ላገኙና ተመሳሳይ የትምህርት ደረጃ ላላቸው ሁሉ:: ከእነዚህ በማስታወሻ 1 እና ዕዝል 2 ከተዘረዘሩት መሆን አለበት::

25 ከዲግሪ በላይ፣ በዩኒቨርስቲ /በኮሌጅ ወይም በተመሳሳይ ተቋም የመጀመሪያ ዲግሪ ካገኙ በኋላ በድህረ ምረቃ ፕሮግራም የማስተርስ ወይም የዶክትሬት ዲግሪ ላገኙ ወይም በድህረ ምረቃ ፕሮግራም ቢያንስ የአንድ ዓመት ትምህርት ላጠናቀቁ፣

95 መሠረተ ትምህርት፣ በመሠረተ ትምህርት ኘሮግራም ማንበብና መፃፍ ችለው በሌላ ቦታ ትምህርት ላልቀጠሉ ሁሉ፣

96 መደበኛ ያልሆኑ፣ በቄስ፣ በቁርዓንና በመሳሰሉት ትምህርት ቤቶች በመማር

ማንበብና መፃፍ የሚችሉ /ትምህርታቸው ወደ መደበኛ የትምህርት ደረጃ አመዳደብ ሊተረጐም የማይችል/እንደዚሁም በራሳቸው ጥረት የግለሰቦችን ዕርዳታ እየጠየቁ ማንበብና መፃፍ የቻሉ ምንም እንኳን በዓምድ 15 ኮድ 1 ቢሞላላቸውም እዚህ ይመደባሉ፡፡ በተጨማሪም በመደበኛ ት/ቤት አንደኛ ክፍል ያላጠናቀቁ ሆነው ወይም በመዋዕለ ህፃናት እየተማሩ ያሉ ነገር ግን ማንበብና መፃፍ የሚችሉ በዚህ ክፍል ይካተታሉ፡፡ እንዲሁም የመሠረተ ትምህርት በመከታተል ላይ የሚገኙ/ኘ ሮግራሙን ያላጠናቀቁ/ ሆነው ማንበብና መፃፍ የሚችሉትንም ያጠቃልላል፡፡